## መንፈሳዊ የጦር ዕቃዎችን መልበስ ኤፌ 6፡12-18፣ 2ቆሮ 10፡14፣

በሰማይና በምድር ሁለት በውጊያ ላይ ያሉ መንግስታት እንዳሉ የእግዚአብሔር ቃል ያስረዳል፡፡ እነዚህም የእግዚአብሔርና የዲያብሎስ መንግሰት ናቸው፡፡ በሁለት መንግስታት መካከል ጦርነት ካለ የየመንግስቱ ዜጎች የጦርነቱ ተካፋዮች መሆናቸው የግድ ነው፡፡ ሲለዚህ የእግዚአብሔር መንግስት ዜጎች የሆንን ሁሉ አወቅነውም አላወቅነው ምን ጊዜም ከዲያብሎስ መንግስት ጋር ጦርነት ላይ ነን፡፡ የሚዋጋን ጠላት ደግሞ ከአጠቃላዩ የእግዚአብሔር መንግስት ዜጋ መካከል በተለያየ ጊዜ የከፋ/የላቀ ውጊያ የሚከፍትባቸው ሰዎች አሉ፡፡ እነዚህ ውጊያ የሚከፈትባቸው የወንጌል አገልጋዮች ብቻ ሳይሆኑ ተራ በተራ ሁሉንም የወንጌል አማኝ የሚያጠቃልል ነው፡፡ ይህ የውጊያ ጊዜ/ቀን መጽሐፍ ቅዱስ ክፉው ቀን ይለዋል፡፡

የሚዋጋን ጠላት ስጋ ለባሽ ሳይሆን መንፈስ የሆነ ቁሳዊ አካል የሌለውና በእዝ ሰንሰለት በረቀቀ ሁኔታ የተደራጀ ስለሆነ የጦር ዕቃችንም መንፈሳዊ መሆን አለበት፡፡ ጠላት ውጊያ የሚከፍተው በአንድ ነገራችን ብቻ ሳይሆን በሕይወታችንና ከእግዚአብሔር በተሰጠን በረከት ሁሉ ላይ ስለሆነ እኛም መልበስ ያለብን ሙሉ የውጊያ መሳሪያዎቻችንን ሁሉ ነው፡፡ የሚዋጋን ኃይል ቀለል አድርገን የምናየው አይደለም፡፡ ውጊያው የሞት ሽረት ውጊያ ነው፡፡ ጠላት የሚዋጋን አልፎ አልፎ ሳይሆን በተከታታይ ቀንና ሌሊት ያለማቋረጥ ነው፡፡ ራዕ 12፡10

- 2ቆሮ 2፡14፤ (ማቴ 28፡18፤) እግዚአብሔር ሁል ጊዜ በሁሉ ስፍራ የክርስቶስ ኢየሱስ አሸናፊነት በህይወታችን እንዲገለጥ አድርጎናል፡፡

ይህም ማለት በእኛ የሚሰራው ኢየሱስ ስልጣን በሰማይና በምድር ሁሉ የኔ ስለሆነ እናንተ ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱና አሸናፊነቴን የሰጠኋችሁን ተልእኮ በመፈጸም ግለጡ ማለቱ ነው፡፡

ኢየሱስ ሰይጣንን ያሸነፈው፡-

ሀ. በምድረበዳ አርባ ቀናት ከጾመ በኋላ በሰይጣን በተፈተነ ጊዜ ... ይሄ ለራሱ ያሸነፈው ነው፡፡

ለ. በመስቀል ላይ ስለ እኛ ተሰቅሎ በመሞት ያሸነፈው በእኛ ፈንታ ሆኖ ነው፡፡ በእርሱ አሸናፊነት እኛ አሸናፊዎች ተደርገናል፡፡ ድሉ ለኛ ነው፡፡ ክርስቶስ ኢየሱስ ዲያብሎስና የጭለማው ኃይል ሰራዊት ሁሉ ሙሉ በሙሉና ለዘላለም አሸንፏል፡፡ ለማሸነፋችን ቁልፍ ነገር ስለሆነ ሰይጣን ይህን እውነት እንድናውቀው አይፈልግም፡፡ ይህን ዕውነት የሚያረጋግጥልን ቃል እንዲህ ይላል፡፡ ቆላ 2፡15፣ "የአለቆችንና የባለ ሥልጣናትንም ማዕረግ በመግፈፍ በመስቀሉ ድል ነሥቶ በአደባባይ እያዞራቸው እንዲታዩ አደረገ፡፡"

ሐ. ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ የድሉ ጉዳይ ምንም ሳይቀር አጠናቆ ስለጨረሰው የሚቀረው የኛ ድርሻ የሆነው ድሉ የራሳችን ማድረግና መጠቀም/ስራ ላይ ማዋል ጉዳይ ነው፡፡ አሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ያገኘነው አሸናፊነት ለዓለም መግለጥ ያለብን እኛ ነን፡፡

ዋነኛው የጠላት የውጊያ ስፍራ አእምሮ ነው፡፡ የእኛ ስራ በክርስቶስ ያላመኑ ሰዎች ሳያውቁት እውነት መስሎዋቸው በአእምሯቸው ተቀብለው ያሰረጹት (በአእሞራቸው የሞላ) ከጠላት የሆነና፣ ሰው ሰራሽ ትምህርትና የአለማወቅ ምሽግ በጸሎት አፍርሰን የእውነት ወንጌል ዘር መዝራት ነው፡፡ ከነዚህ ዓይነት ሰዎች ጋር መከራከር አለማመናቸውን ቢያባብሰው እንጂ አያስተካክለውም፡፡ ይህን ምሽግ ማፍረስ የሚችለው ምን ዓይነት የጦር መሳሪያ እንደሆነ የእግዚአብሔር ቃል በ2 ቆሮ 10፡3-5፣ ኤር 1፡10፣ ይገልጻል፡፡ እግዚአብሔር እነዚህን ምሽጎች የምናፈርስበት ራሳችንም የምንከላከልበትና ጠላትን የምናጠቃበት የጦር መሳሪያዎች ሰጥቶናል፡፡ የእግዚአብሔር ቃል በእምነት ተቀብለን ከሰራንበት ማንም የማይቋቋመው መለኮታዊ ኃይል ያለው ስለሆነ በዓይን የሚታይ ተጨባጭ ውጤት በማስገኘት ይሰራል፡፡

*2 ቆሮ10፡3-5፣ "የምንኖረው በዚህ ዓለም ቢሆንም፣ የምንዋጋው በዚህ ዓለም ስልት አይደለም።[4] ደግሞም የምንዋጋበት የጦር መሣሪያ የዚህ ዓለም መሣሪያ አይደለም፤ ይሁን እንጂ ምሽግን ለመደምሰስ የሚችል መለኮታዊ ኀይል ያለው ነው። [5] በእግዚአብሔር ዕውቀት ላይ በትዕቢት የሚነሣውን ክርክርና ከንቱ ሐሳብ ሁሉ እናፈርሳለን፤ አእምሮንም ሁሉ እየማረክን ለክርስቶስ እንዲታዘዝ እናደርጋለን።"*

*2 ቆሮ 6፥7፣ "በእውነት ቃል፣ በእግዚአብሔር ኀይል፣ በቀኝና በግራ እጅ የጽድቅ የጦር ዕቃ በመያዝ፣"*

*ኤር 1፥10፣ "እንግዲህ፣ እንድትነቅልና እንድታፈርስ፣ እንድታጠፋና እንድትገለብጥ፣ እንድታንጽና እንድትተክል በአሕዛብና በመንግሥታት ላይ ዛሬ ሾምሁህ።"*

- ራዕ 12፡10፣ ጠላት በእግዚአብሔር ፊት በመቅረብ የሚከሰን ብቻ ሳይሆን እርስ በራሳችንና በሌሎች ሰዎች የሚከሰን የበደለኝነት/የኃጢአተኝነት ስሜት እንዲሰማን /እንድናስተናግድ/ ነው። ስለዚህ ደጋጋመን ራሳችን የምንኮንን ከሆነ ለጠላት ውጊያው ተሸናፊዎች እንሆናለን። ጻድቅነት ለድላችን ቁልፍ ነገር ሲሆን በደለኝነት ደግሞ ለሽንፈታችን ቁልፍ ነው።

እግዚአብሔር ስለዚህ በደለኝነት /ኃጢአተኝነት/ ጉዳይ በመስቀል ላይ ያደረገው ምንድነው?

ስላለፈው በደላችን፣ ቆላ 2፡13፣ *"... እግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር ሕያዋን አደረጋችሁ፤ ኃጢአታችሁንንም ሁሉ ይቅር አለን።"*

ስለወደፊቱ፣ 2፡14፣ *"ሲቃወመንና ሲጻረረን የነበረውን የእዳ ጽህፈት ከነ ሕግጋቱ በመደምሰስ በመስቀል ላይ ቸንክሮ ከመንገድ አስወገደው።"*

2 ቆሮ 5፡21፣ *"እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንድንሆን ኃጢአት የሌለበትን እርሱን እግዚአብሔር ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው።"*

ሮሜ 3፡21-22፣ *"አሁን ግን ሕግና ነቢያት የመሰከሩለት፣ ከሕግ ውጭ የሆነ፣ የእግዚአብሔር ጽድቅ ተገልጦአል። [22] ይህ የእግዚአብሔር ጽድቅ ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን የሚገኝ ጽድቅ ነው። ልዩነት የለም፤"*

***የጦር መሳሪያዎቻችን የመከላከያና የማጥቂያ መሳሪያዎች ናቸው።***

1. **የእውነት ዝናር** (Belt of truth) ፦ ኢሳ 11፡5
   ዘፍ 3 ላይ ሰይጣን ሄዋንና አዳምን አሳተ። ዮሐ 8፡44፣ እርሱ ውሸታምና የውሸት አባት መሆኑ ይገልጻል።
   ስለዚህ ዝናር የሰይጣንን ማሳት፣ ውሸትና የሚዘራውን ጥርጣሬ የምንቋቋምበት ነው።

   *መጽሐፍ ቅዱስ* የእግዚአብሔር *ቃል* እውነት እንደሆነ ያስረዳል፡ - *መዝ* 33፡4፣ 119፡160፣ ኢሳ 45፡ 19፤ የሐ 17፡17፤
   ጌታ ኢየሱስ "*መንገዱ* እኔ ነኝ፣ እውነትና ሕይወትም እኔው ነኝ፣..." ብሏል። ዮሐ 14፡6፤
   እግዚአብሔርም "የእውነት አምላክ"፣ መንፈስ ቅዱስም "የእውነት መንፈስ" ይባላሉ።
   ዮሐ 8፡32፣ "እውነትን ታውቃላችሁ፣ እውነትም ነጻ ያወጣላችኋል" ይላል።
   የእውነት ዝናር መታጠቅ ማለት የእግዚአብሔርን ቃል በጥንቃቄ በማጥናትና በማወቅ እያደጉ ጠላት ለማታለልና ለማሳት በተለያየ መልኩ የሚያቀርበውን ውሸት አለመቀበል ማለት ነው። እንዲሁም የእውነት ቃል ምንጭ የሆነው እግዚአብሔር አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ማንነት ጠንቅቆ በመረዳት በሀሰተኛ የትምህርት ነፋስ ከመወሰድ ከንቱ አማልክትን ከመከተል መራቅ ነው። ኤፌ 4፡14-15፣ ቆላ 3፡16

ብዙዎች ሐዋርያው ጳውሎስ የጦር መሳሪያዎቹን ሲዘረዝር በወቅቱ አስራኤልን የወረሩት ሮማውያን ይጠቀሙበት የነበሩ መሳሪያዎች ሁሉ የሚመስሉ መንፈሳዊ መሳሪያዎችን ነው የጠቀሰው ይላሉ። ነገር ግን እነዚህ የጦር መሳሪያዎች ጥንታዊያን እስራኤላዊያን ይጠቀሙባቸው እንደነበረ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ሰፍሮ ይገኛል። (አንዴ ታጥቀናቸው እዚያው ቦታቸው ላይ የሚቆዩት ዝናር፣ ጥሩር፣ ጫማና የራስ ቁር ከኢሳያስ መጽሐፍ የመጡ ሲሆኑ ተንቀሳቃሽ የሆኑት ጋሻና ሰይፍ ከንጉስ ሰለሞን ጽሁፎች የመጡ ናቸው።)
በወቅቱ የሚለብሱት ልብስ ከላይ ጀምሮ ወደ እግር የሚወርድ ወጥ የሆነ ሰፋ ያለ ቀሚስ አይነት ስለነበረ በውጊያ ወቅት እያወላከፈ/እየጠለፈ እንዳያስቸግር በነጻነት ሌሎቹን መሳሪያዎች በመጠቀም መዋጋት እንዲያመች በወገብ ዝናር ሰብስቦ ሸብ ይደረግ ነበር። የእኛ መንፈሳዊ ዝናር እውነት ነው። ይህም በሁለት ክፍለን የምናየው ነው።
ሀ. ሰይጣን ስለ ራሳችንና ስለ እግዚአብሔር ማንነት፤ ስለ መዳንና መባረክ መንገድ በማሳት ጥበቡ ሊያስት ሲሰራ የእግዚአብሔርን ቃል ተግተን በማጥናትና በማወቅ ቃሉ የሚለንን አምነን በመጽናት መመከትና ከመሳት መጠንቀቅና መጠበቅ ነው። ዘፍ 3፣ ማቴ 24፡12፣ የሐ 8፡44፣ ጠላት የሚያስተው ከእግዚአብሔር ያልሆነ ውሸትን በማስተማር በማታለልና በማሳት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ዕውነት መሆኑን የሚገልጸው የእግዚአብሔርን ቃል ነው። ዮሐ 8፡32፣

ለ. በግላችን በተማርነው የእግዚአብሔር ቃል እውነት መሰረት በቅንነትና ታማኝነት ተላብሰን፣ ቅጥፈትን በማስወገድ መኖርን የሚያሳይ ነው። ኤፌ 4፡25፣ ስለዚህ ውሸትን አስወግዳችሁ ከባልንጀራችሁ ጋር እውነትን ተነጋገሩ ይላል።
ይሄ እውነት በዕለት ተዕለት ሕይወታችን የሚገለጥ እውነት ነው። በምንተገብረው ተግባራችን ሁሉ እውነትን መናገር/አለመዋሸት- ንግራችን አዎን ከሆነ አዎን፣ አይደለም ከሆነ አይደለም ማለት ነው፤ ታማኝነት፤ ሰው በሚያይ ሥፍራ ጨዋ መምሰል ሰው በሌለበት ሥፍራ ግን ያልተገባ ነገር መነካካት አይገባም። የሀሰት ሚዛን አለመጠቀምን ...ወዘተ የሚያመለክት ነው።

2. **የጽድቅንም ጥሩር** ለብሳችሁ (Breastplate) ኢሳ 59፡17፡-
ማቴ 4፡3፣ ሰይጣን ፈታኝ እንደሆነ ይናገራል። የተለያየ ከኑሮ ጋር በተያያዘ ለዓይን የሚስብ፣ ልብን የሚያማልል ነገር በማቅረብ፣ ምንም ሳይኖር እንኳ በማስታበይ ሳይቀር ለእርሱ ጥቃት በር ለማስከፈት ይሰራል።

ይኸውና በዚህና በዚያ ጉዳይ፣ ተግባርህ ኃጢአተኛ ስለ ሆንህ አግዚአብሔር ካንተ ጋር አይደለም፣ ጸሎትህንም አይሰማም የሚሉና የመሳሰሉ ክሶችና ተስፋ የሚያስቆርጡ ሁኔታዎች በማቅረብ እንድንጠራጠር፣ እንዳንነቃቃ ሲሰራ አለመቀበል ነው።
ጥሩር የሚለበሰው ለደረት ነው። በደረት ውስጥ ደግሞ እጅግ በጣም አስፈላጊ የሆነ የሰውነት ብልት ልብ አለ። ይህ ልብ ጠላት በሚያመጣው ፈተና እንዳይጠቃ መጠንቀቅ አለብን።

ስለ ጽድቅ የመጀመሪያው ነገር ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ በመመልከት እርሱ ለእኛ በሰራው የጽድቅ ስራ በእግዚአብሔር ፊት ጽድቃችን ተደርጎ መቆጠሩን በእምነት መያዝ ነው። ፊሊጵ 3፡9 ሕግ በመጠበቅ የሚገኝ የራሴ ጽድቅ ኖሮኝ ሳይሆን በክርስቶስ በማመን ይኸውም ከእግዚአብሔር የሚመጣ ከእምነት በሆነ ጽድቅ በእርሱ ዘንድ እንድንገኝ ነው።
ሮሜ 5፡17-18፣ 3፡21-22፤ 2ቆሮ 5፡21፣ የኔ ጽድቅ የመጣው ክርስቶስ ኢየሱስ በምድር በተመላለሰበት ወቅት የኖረው ማንም የማይደርስበት እንከን አልባ ጽድቅ ለኔ ስጦታ ተደርጎ ስለተሰጠኝ

ነው ብሎ በማመን የሚገኝ ነው። ፍጹም ጽድቅ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ በሰው ጥረት የሚገኝ አይደለም።
ሮሜ 10፡4፣ "ለሚያምን ሁሉ ጽድቅ ይሆን ዘንድ ክርስቶስ የህግ ፍጻሜ ነውና።" ክርስቶስ የህግ ፍጻሜ የሆነው የሙሴ ህግን ለመሻር አይደለም። የአዲስ ኪዳን ዘመን ሰዎች የምንጸድቀው በስራ ህግ ሳይሆን በእምነት እንዲሆን ነው። በእግዜአብሔር ፊት ጻድቅ ለመሆን በክርስቶስና በእርሱ የተሰራልንን ማመን እንጂ የሙሴን ሕግ መፈጸም አይጠይቀንም።
ሮሜ 5፥17፣ "…የእግዚአብሔርን የተትረፈረፈ ጸጋና የጽድቅ ስጦታ የተቀበሉት፣ በአንዱ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እንዴት አብልጠው በሕይወት አይነግሡ!"

እምነት ስንል እንዲያው ባዶ እምነት ሳይሆን በፍቅር የሚገለጽ የሆነና የሚሰራ እምነት ነው። በተሰራልን ስራ ያለን እምነትና ለጌታ የምናሳየው ፍቅር በአንድነት አጣምሮ የያዘ መከላከያ ነው ልባችንን በአስተማማኝ ሁኔታ ከጠላት ከጥቃት የሚጠብቀው።
ስለዚህ 1ተሰ 5፡8፣ "እኛ ግን የቀን ሰዎች ስለሆንን እምነትና ፍቅር እንደ ጥሩር ለብሰን…ራሳችንን በመግዛት እንኑር፣" ይላል፤
ያዕ 4፡7-10 እንግዲህ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አስገዙ ዲያብሎስን ተቃወሙት፣ ከእናንተም ይሸሻል ወደ እግዚአብሔርም ቅረቡ እርሱም ወደ እናንተ ይቀርባል።…ስለሚል፤ (ሮሜ 8፡12-14)፣
ማቴ 7፡24-27፡ - እኛም እምነታችንን በተግባር በማሳየት ወደ ፍጹምነት ደረጃ የደረስን ባይሆንም የእግዚአብሔርን ቃልና የመንፈስ ቅዱስን ምሪት በመታዘዝ ፍሬ እያፈራን ከጊዜ ወደ ጊዜ እድገት/ብስለት እያሳየን መሄድ ይገባናል። ይህን ካደረግን ነው ጌታ እምነታችን እውነተኛ መሆኑ ማረጋገጫ ስለሚያይበት የሚያስፈልገንን ጸጋ በመስጠት የጠላትን ሰልፍ መቋቋምና ጸንተን መቆም የሚያስችል አቅም የሚሆነን። ለእግዚአብሔር ቃልና ለመንፈስ ድምጽ/ምሪት በታዘዝን መጠን ነው በጠላት ውጊያ ወቅት ኃይል/ድል የሚኖረን። ኤፌ 4፡22-32
ሐዋሪያው ጳውሎስ እንደ እግዚአብሔር ሰራተኞች፤ 2ኛ ቆሮ 6፡6-7፣ "በንጽሕና፣ በዕውቀት፣ በትዕግሥት፣ በቸርነት፣ በመንፈስ ቅዱስ፣ በእውነተኛ ፍቅር፣ [7] በእውነት ቃል፣ በእግዚአብሔር ኀይል፣ በቀኝና በግራ እጅ የጽድቅ የጦር ዕቃ በመያዝ፣…" ኖረናል ይላልና እኛም ይህንኑ መልካም አርአያነት መከተል ነው።

3. **በሰላም ወንጌል መጫማት፡-** (Good news of peace ኢሳ 52፡7)
   ማቴ 13፡39፣ ዘርቶ የሄደውም ጠላት ዲያቢሎስ ነው። ዲያቢሎስ ጠላት ተብሏል። ጠላታችን የወንጌልን ዕውነት ይጠላል። ስለዚህ በተቻለው ሁሉ በወንጌል ሰላም እንዳናርፍና ወንጌልን ለሌሎች እንዳናሰማ ይዋጋል።
   *ሀ.* በወንጌል ባገኘነው ሰላም ማረፍ፡- ሮሜ 5፥1 "እንግዲህ በእምነት ስለ ጸደቅን፣ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም አለን።"
   ዮሐ 14፥27 "ሰላምን እተውላችኊለሁ፤ ሰላሜን እሰጣችኊለሁ፤ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጣችሁ አይደለም። ልባችሁ አይጨነቅ፤ አይፍራም።"
   ሰላምን በጫማ የተመሰለው ወደ ጦር ሜዳ የሚገባ ወታደር በመንገዱ ላይ ያሉ ሹል ጠጠሮችና እንቅፋቶች ይጎዱኛል ብሎ ትኩረቱን በእነርሱ ላይ ከደረገ፣ ዋናው ትኩረቱ ዋናና አደገኛ ከሆነው የሚዋጋው ጠላት ላይ አንስቶ በጥቃቅን ነገሮች ላይ በማድረጉ ተጠቅቶ ሊሸነፍ ነው። ክርስቲያንም በኑሮ ውጣውረድና በጥቃቅን ነገሮች ጭንቀት፣ በጌታ ወደ ማጉረምረም፣ ስጋት ሁከት ውስጥ እንዲገባ አጋንንት ይሰራሉ። ይህ ደግሞ ሰይጣንና አጋንንቱን የማሸነፍ ዕድል የሚሰጣቸው ነው።

ስለዚህ ስለ ሁሉ ነገር ጌታን እያመሰገኑ የሚያስጨንቁ ነገሮች ሁሉ በመዘርዝር በጌታ ፊት ጥሎ/አቅርቦ በመተው፣ በወንጌል ሰላም በማረፍ ትኩረትን ጠላትን በመዋጋት ላይ ማድረግ ነው፡፡

ለ. ኢሳ 52፡7፣ ይሄ ዝግጁ ሆኖ መገኘት የሚያመለክተው መጽሐፍ ቅዱስን በማጥናት የወንጌል መልእክትን በማወቅና በማስታወስ ያወቅነውን የወንጌል እውነት በማንኛውም ጊዜ ለሌሎች ለማካፈል/ለማስረዳት ብቁና/ዝግጁ ሆኖ መገኘት ነው፡፡ ራሳችን በምንና እንዴት እንደዳንን ሌሎች ሰዎችም እንዴት ሊድኑ እንደሚችሉ ማሳየት ነው፡፡ በማንኛውም ስፍራና ጊዜ የወንጌል መልእክት ሊሰሙ የሚያስፈልጋቸው ሰዎች ሲያጋጥሙ ለመመስከር ለጌታ ዝግጁ ሆኖ በመገኘት፣ የተገኙ ምቹ አጋጣሚዎችን ሁሉ መጠቀምና መመስከር እንደሚገባ ያሳያል፡፡ በውትድርና ህይወት ጠላት በቅርብ ርቀት የሚገኝ ከሆነ ቀኑ መሽቶ ሲተኙ እንኳ ጫማ ሳያወልቁ ከተኙ ጠላት ድንገት ጥቃት ቢከፍት ጫማ ፍለጋና ማጥለቅ ማሰርም ሳያስፈልግ በቀጥታ ወደ ውጊያ መግባት ያስችላል፡፡

4. **የእምነት ጋሻ መያዝ** (Shield of faith) መዝ 144፡2
ጋሻ በቅርጹ ሁለት ዓይነት ነው፡፡ የመጀመሪያው ክብ ቅርጽ ያለው መጠኑም አነስተኛ ስለሆነ አነስተኛ የሰውነት ክፍልን መከለል የሚችል ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ የበር ቅርጽ ዓይነት ሬክታንጉላር ሆኖ ሙሉ ሰውነትን የሚከልል ነው፡፡ ይሄ ዓይነቱ የእምነት ጋሻ አንድ ሰውን ብቻ ሳይሆን መላው ቤተሰብንና ንብረትን ሁሉ ከጠላት ጥቃት የሚከልል ነው፡፡
ጠላት የሚመጥነው የሌለው ክፉ ስለሆነ ስደት በማስነሳት፣ ጥርጣሬ በመሙላት፣ በስህተት አስተማሪዎች፣ የተለያዩ በሽታዎች ላይ በመጣል፣ በህልም በማወክ፣ ፈተና ውስጥ በማስገባት፣ ደካማ ጎኖችህን በመጠቀም… ይዋጋል፡፡
ጠላት ጥርጣሬ ሲወረውር እምነት አንጥሮ ይመልሰዋል፡፡ ፈተናም ሲመጣ ያመንነውን ስለምናውቅ እምነት አጽንቶ ያቆማል፡፡ እስራኤላዊያን በግብጽ ምድር በያንዳንዱ ግብጻዊ ቤት በኩር በሚቀሰፍበት ቀን በእምነት በቤታቸው መቃንና ጉበን የቀቡት የጥቦት ደም ቤቱ ውስጥ ያለውን ሁሉ ከቀሳፊው ኃይል እንዳዳነ የሚያድን ነው፡፡
ኢዮ 1፡10፣ ኢዮብ ራሱና ቤተሰቡ ብቻ ሳይሆን የነበረው ሀብትና ንብረት ሁሉ ከጠላት ጥቃት የታጠረለት በእግዚአብሔር ላይ በነበረው እምነት ነው፡፡
በእምነት የክርስቶስን ደም በራሳችንና የራሳቸን በሆነው ቤተሰብ አባላት ሕይወትና በረከት ሁሉ በየቀኑ በእምነት ብንረጨው በአግዚአብሔር ቃል መሰረት ሁሉ ነገራችን ከጠላት ይጠበቃል፤

ይህ እምነት የመጣው ከራሳችን አይደለም እግዚአብሔር ስለሰጠን ነው እንጂ፡፡ ሮሜ 12፡3፣ በተሰጠን እምነት ከጌታ ጋር መራመዳችን ስንቀጥል ያ እምነት ወደ ጋሻነት ያድጋል፡፡ ጠላት የሚወረውራቸው ጥርጣሬ፣ ውሸትና ክፉ አሳብ ሁሉ መመከቻ ነው፡፡ ስለዚህ

- የሰይጣንን ማንነትና የተንኮል አሰራርን፣ የጥቃት ስልቱን ማወቅ፣
- ፍላጻዎች በመወርወር አንተን ሊያጠቃ ምቹ በር የሚከፍትለት ደካማ ጎንህን ማወቅና መጽሐፍ ቅዱሳዊ የመፍትሄ እርምጃ መውሰድ፡፡ መወገድ ያለበትን አስወግድ፤
- የእግዚአብሔር ኃይልና ችሎታ ወሰን አልባ ታላቅነት የበላይነቱን ጥበቃውን የሚገልጹ ጥቅሶች በማሰላሰልና በማወጅ በእግዚአብሔር ማዳን መታመን፡፡
- ወደ አእምሮህ የሚመጡ አሳቦች በመመርመር፡ - ይህ እውነት ነውን፣ እግዚአብሔርን የሚያከብርና እምነቴን የሚያንጽ ነውን፤ ንጹህ ነውን፤ ካልሆነ በሱ ላይ ጊዜህን በማጥፋት ለጠላት በር ላለመክፈት አለማተናገድ ነው፡፡ ለምሳሌ ጥርጣሬ የምታስተናግድ ከሆነ በአግዚአብሔር ቃልና በእግዚአብሔር ማንነት አምነህ ጽና፡፡

5. **የመዳን ራስ ቁር** (Helmet of Salvation) ኢሳ 59፡17፣ ኤፌ 6፡17፡-

የራስ ቁር የሚከላከለው ራስን (አእምሮና፣ አስተሳሰብን) ነው፡፡
ጭንቅላት ውስጥ የሚገኘው አእምሮ ነው፡፡ አእምሮ ጠላት ውጊያ የሚያደርግበት ዋነኛ ስፍራ ነው፡፡ አእምሮ ከተጎዳ ሌሎች የውጊያ መሳሪያዎችን አቀናጅቶ መጠቀም አይቻልም፡፡ 1ተሰ 5:8፣ አእምሮዋችንን እንደ ራስቁር የምንጠብቀው በተስፋ ነው፡፡ አእምሮ ካልተጠበቀ ግን ለዲፐሬሽንና ለመሳሰሉት የጠላት ውጊያዎች ተጠቂ ይሆናል፡፡ በእምነትና በተስፋ መካከል ያለው ግንኙነት በጽኑ እምነት ላይ የተመሰረተ ከሆነ ተስፋም የጸና ነው የሚሆነው፡፡

ተስፋ ቀጣይነት ያለው የማይወላውል ድነትን ጨምሮ ብዙ መልካም የእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች ይሆኑልኛል ብሎ በትእግስት እና በእምነት በመጽናት መጠበቅ ነው፡፡ (ኤክስፔክቴሽን).
ኔጋቲቭ/አሉታዊ አስተሳሰብን በፖሰቲቭ/አዎንታዊ አስተሳሰብ ለውጠን መልካም ይሆንልኛል ብለን ተስፋ ማድረግ ከእኛ የሚጠበቅብን ነው፡፡
ሰቆ ኤር 3:26 ሰው የእግዚአብሔርን ማዳን ተስፋ በማድረግ በትዕግስት ቢጠባበቅ መልካም ነው፡፡ (It is continuing optimism in the promises of God.)
ሮሜ 8:25 “ነገር ግን ገና ያላየነውን ተስፋ ብናደርግ፣ (በእምነት ጸንተን) በትዕግሥት እንጠብቀዋለን።” ተስፋ ሁል ጊዜ ወደፊት የሚሆነውን ነገር ነው የሚያመለክተው፡፡
ራዕ 21:1-5፣ 22-27 በእነዚህ ጥቅሶች እግዚአብሔር ከአእምሮ በላይ ታላቅ የሆነ ዋጋ የያለው ተስፋ ሰጥቶናል፡፡
ተስፋ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ለህዝቡ ወደፊት አደርገዋለሁ ያለው እጅግ አስደናቂና መልካም ነገር ሁሉ ይፈጸማል ብሎ በጽኑ እምነትና በትዕግስት መጠባበቅን ነው፡፡
ሰይጣን ከያዝነው እምነትና ከምንመካበት አግዚአብሔር ለማራቅ የሚጠቀምበት የተለያየ ስልፍ እንዲሁም የምድራዊ ኑሮ ውጣውረድ መቋቋም የሚያስችለን የራስ ቁር ይሄ ተስፋችን ነው፡፡ የተዘጋጀልንን ዘላለማዊ ክብር ሳንወርስ ለማስቀረት የሚገጥሙን ጊዜያዊ መከራዎችና ውጊያዎች ሁሉ እንደ ቀላል ነገር በመቁጠር ራሳችንን ከጉድፍ ሁሉ በመጠበቅ ቀጣይ ሩጫችንን ለመሮጥ የሚያስችለን አቅም ይሄ ተስፋ ይሰጠናል፡፡ ይሄ የራስ ቁር ካለን ሰይጣንም በተለያዩ ፈተናዎች አሰናክሎ መጣል አይሆንለትም፡፡

ኤፌ 2:12፤ ቆላ 1:27፤ ክርስቶስ በውስጣችሁ ካለ ተስፋ አላችሁ፡፡ ዕብ 6:17-19፤ ሮሜ 8:24 ተስፋ ከሌለ መዳን የለም፡፡ በኢየሱስ ክርስቶስ አምኖ የመዳን ተስፋ አንድ ነገር ብቻ የያዘ ሳይሆን የብዙ በረከት ዝርዝር አጠቃሎ የያዘ ፓኬጅ ነው፡፡ ይህ ድነት አካላዊና መንፈሳዊ ጤንነታችን፣ ስራችንና አገልግሎታችን ፍሬያማነት፣ ለእግዚአብሔር ክብር በአገልግሎታችን የምንጠቀምባቸው መንፈሳዊና ሌሎች ስጦታዎችን፣ እንዲሁም የዘላለም የክብር ሕይወትን..ያጠቃልላል፡፡ እምነትና ተስፋ እርስ በርስ የተያያዙ ነገሮች ናቸው፡፡

ዮሐ 10:27-30፣ "በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ፤ እኔ ዐውቃቸዋለሁ፤ እነርሱም ይከተሉኛል፤
[28] እኔ የዘላለም ሕይወት እሰጣቸዋለሁ፤ ከቶ አይጠፉም፤ ከእጄም ሊነጥቃቸው የሚችል ማንም የለም። [29] እነርሱን የሰጠኝ አባቴ ከሁሉ ይበልጣል፤ ከአባቴም እጅ ማንም ሊነጥቃቸው አይችልም። እኔና አብ አንድ ነን።" (ይህን ጥቀስና የመሳሰሉት በቃል በማጥናት ጠላት ሲፈታተን በእምነት መናገር ነው፡፡)
2ኛ ቆሮ 10:3-5፣ "የምንኖረው በዚህ ዓለም ቢሆንም፣ የምንዋጋው በዚህ ዓለም ስልት አይደለም።[4] ደግሞም የምንዋጋበት የጦር መሣሪያ የዚህ ዓለም መሣሪያ አይደለም፤ ይሁን እንጂ ምሽግን ለመደምሰስ የሚችል መለኮታዊ ኀይል ያለው ነው። [5] በእግዚአብሔር ዕውቀት ላይ በትዕቢት

የሚነሣውን ክርክርና ከንቱ ሐሳብ ሁሉ እናፈርሳለን፤ አእምሮንም ሁሉ እየማረክን ለክርስቶስ እንዲታዘዝ እናደርጋለን።"

6. **የመንፈስ ሰይፍ** (Sword of the Spirit) ፦ ይህ መሳሪያ መመከቻ ብቻ ሳይሆን ማጥቂያም ነው። እንደ ማጥቂያ የምንጠቀመው በተለይም ወንጌልን ሌሎች እንዲድኑበት ስንመሰክር ነው። ይህም መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብርን መንግስት ለማስፋት ይጠቀምበታል።
   *በመከላከያ መሳሪያነት* - ጠላት ውሸትና የማሳቻ ጥቃት ሲከፍትብን ስለዚያ ጉዳይ ጌታ ኢየሱስ እንዳደረገው የእግዚአብሔር ቃል የሚለውን ምላሽ በመስጠት ጠላትን ለመመከትና የአጸፋ ምላሽ በመስጠት እንዋጋበታለን።

   ጠላትን ከህይወታችንና ከበረከታችን የምናርቅበት መሳሪያ የእግዚአብሔር ቃል/የእምነት ቃል ነው። ከመጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ቃል ወስደን በአፋችን በእምነት ስንናገረው የእምነት ቃል/የመንፈስ ሰይፍ ይሆናል። መጽሀፍ ቅዱስ በቀድሞ ዘመናት ሲነበብ ጸጥ በማለት ሳይሆን ድምጽ አሰምቶ በመናገር ነበር። ሐሥ 8፡30፤

   **ተጨማሪ የማጥቂያ መሳሪያዎች**

7. **ጸሎት** ሐሥ 12፡1-23፣ ከማናቸውም መሳሪያዎች ይልቅ በየትኛውም ስፍራ በሰማይና በምድር ሁሉ ርቀት ሳይወስነው የሚሰራ ኃይለኛ መሳሪያ ነው። በጸሎት፣ ታስሮ የነበረው ሐዋሪያው ጴጥሮስ ተፈታ። አጥብቆ መጸለይ የእግዚአብሔር መላእክት ሳይቀር ጣልቃ ገብተው እንዲሰሩ ያስችላል። በዳንኤል ዘመንም የመላእክት ጣልቃ ገብነት ያስከተለው ጥብቅ ጸሎት ነው። ሐዋሪያትን ማስገደል የጀመረው ንጉስ ሄሮድስ በእግዚአብሔር መልአክ ተቀስፎ በትል ተበልቶ እንዲሞት ሆነ። በወንጌል በማያምኑት ሰዎች አእምሮ የሞላውን የሐሰትና ሰው ሰራሽ ትምህርት ምሽግ ለማፍረስም ትልቅ መለኮታዊ ኀይል የለውም ይኸው ጸሎት ነው።

8. **እግዚአብሔርን ማመስገንና ማወደስ**፦ በመጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር አስፈሪና ኃያል ስራውን ይገለጽበታል። ውዳሴና ምስጋና ጌታ በጉዳያችን ጣልቃ እንዲገባ ያነሳሳል። ጣልቃ ገብቶ ለሰራው ስራም ምላሹ ምስጋና ነው። ሐሥ 16፡24-32
   *መዝ* 8፡2፣ "ከህጻናትና ጡት ከሚጠቡት አፍ በሚወጣ ምስጋናና ውዳሴ አማካይነት ጠላትና ለበቀል የወጣውን ጸጥ የሚያሰኝ ኃይል አዘጋጀህ።"
   *መዝ* 149፡6-9፣ "የአምላክ ውዳሴ በአንደበታቸው፣ ባለ ሁለት ልሳን ሰይፍ በእጃቸው ይሁን። በዚህ ህዝቦችን ይበቀላሉ፤ ሰዎችንም ይቀጣሉ። ነገስታቶቻውን በሰንሰለት መኳንንቶቻቸውን በእግር ብረት ያስራሉ *(በነርሱ ላይ የሚሰሩት አለቃ መናፍስትን ለማለት ነው)*። ይህም በነርሱ ላይ የተጻፈውን ፍርድ ለመፈጸም ነው። ለቅዱሳኑ ሁሉ ይህች ክብር ናት። ሃሌ ሉያ።"
   በ ዘፀ12፡12 እግዚአብሔር የግብጽን በኩር ከመምታቱ በፊት የመታው የግብጽን አማልክት ነው። አማልክቱ ሲመቱ ካገራችን ውጡልን በማለት ወርቃቸውን ሳይቀር በመስጠት ሂዱልን አሏቸው። በገሀዱ ዓለም የሚሆነው በመንፈሳዊው ዓለም የሆነው ነገር ነጸብራቅ ነው።

9. **የእግዚአብሔርን ቃል መስበክ/ማስተማር**፦ 2ጢሞ 4፡1-4፣ ዕብ 4፡12 እነዚህ ጥቅሶች የእግዚአብሔርን ቃል ኃይል ያሳያሉ።
   *ሐሥ* 19፡11-12-16-17-19 ትክክለኛ የእግዚአብሔር ቃል በመሰበኩ ምክንያት የሆኑ ነገሮችን ያሳያል። እግዚአብሔር የተለመዱ ያልሆኑ በጠላት ኃይል ላይ ሙሉ የበላይነቱን የሚያሳዩ አስደናቂ ምልክቶችና ማረጋገጫዎችን የሚያደርገው ትክክለኛ ቃሉ ሲሰበክ ነው። በዚህም በጭለማ ውስጥና በክፉ መናፍስት

እሰራት የነበሩትን ከጠላት እጅ ነጥቆ በማውጣት ማጥቃትና የጌታ ተከታዮች እንዲሆኑ ማድረግን ያስከትላል።

10. **ምስክርነት** (testimony, witnessing) *ሐሥ* 1፡8፣ ምስክርነት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስጋ ለብሶ በምድር በተመላለሰበት ጊዜ አብረውት የነበሩ ደቀመዛሙርት እስከ ሞትና ትንሳኤው ድረስ ሲያደርግ ሲናገርና ሲሰራ ያዩትን የዓይን ምስክርነት ሰጥተዋል፤ እኛ በአሁኑ ዘመን ያለን ክርስቲያኖች ጌታን ከተቀበልን በኋላ በግል ሕይወታችን ያደረገው ነገር መመስከር እንዲሁም በ3ኛነት በመጽሐፍ ቅዱስ የክርስቶስ ኢየሱስ ደም ለኛ አደረገ/ያደርጋል የሚለውን አምነን ተቀብለን ያንኑ መልሰን በአፋችን ማናገርን /መመስከርን/ ያመለክታል። 1ሳሙ 17፡37፣ *ራዕ* 12፡11?
አንዴ ከጠላት ጋር ውጊያ ከጀመሩ በጭራሽ ጀርባን ለጠላት መስጠት/መጠራጠር/ተስፋ መቁረጥ ወይም ወደኋላ ማፈግፈግ አይገባም። ይሄ በመከላከያ ጋሻ የልተሸፈነውን ሰውነታችን ጠላት እንዲያጠቃ ዕድል የሚሰጠው ስለሆነ ለእርሱ ምቹ ሁኔታ ላለመፍጠር መጠንቀቅ ነው።

ኤልያስ ታሪኩ (ዶ/ር)   2019 ዓ.ም.